፲፱

# የሕዝብና ቤት ቁጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

## የወሳኝ ኩነቶች (ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ) ምዝገባና ስታትስቲክስ

*ምንድን ናቸው?*

*እንዴትስ ይገኛሉ?*

*ለምንስ ይጠቅማሉ?*

አዲስ አበባ

ጥር 1996

# የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

## የወሳኝ ኩነቶች (ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ) ምዝገባና ስታትስቲክስ

*ምንድን ናቸው?*

*እንዴትስ ይገኛሉ?*

*ለምንስ ይጠቅማሉ?*

አዲስ አበባ

ጥር 1996

# ማውጫ

1. መግቢያ ........................................ 1
2. በዓለማችን የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ አሠራር
የተጀመረው መቼና እንዴት ነው? ........................................ 2
3. በዓለማችን አግባባዊ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሠራር
የተጀመረው መቼና እንዴት ነው? ........................................ 3
4. ወሳኝ ኩነቶች የሚባሉት እነማን ናቸው? ........................................ 4
5. ኩነቶቹ ወይም ክስተቶቹ ወሳኝ የተባሉበት መሠረታዊ
ምክንያት ምንድን ነው? ........................................ 4
6. የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ትርጉም ........................................ 5
7. የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ ትርጉም ........................................ 5
8. የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት ትርጉም ........................................ 6
9. የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ዓላማዎች ........................................ 6
10. የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ ዓላማዎች ........................................ 7
11. የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባና የስነ-ህዝብ መረጃ
አቅርቦት ........................................ 7
12. ወሳኝ ኩነቶች ግለሰብን ከመንግሥት ጋር እንዴት ያገናኛሉ? ........................................ 8
13. በኢትዮጵያ አግባባዊ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ መኖር
በመንግስት የህግና ማህበራዊ አገልግሎት አሰጣጥ
የሚያስገኘው መረጃና ጥቅም ምንድነው? ........................................ 10
14. በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ያለበት ሁኔታ ........................................ 14
15. በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት በሀገሪቱ የወሳኝ
ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓቶችን ለመዘርጋት ምን
ጥረቶች እየተደረጉ ነው? ........................................ 16
16. የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባና ያልተማከለ የሕዝብ
አስተዳደር ግንባታ ........................................ 17
17. የምዕተ ዓመቱ የልማት ዓላማና የወሳኝ ኩነቶች
ስታትስቲክስ ምዝገባ መረጃ አቅርቦት ........................................ 18
18. ማጠቃለያ ........................................ 19

## 1. መግቢያ

በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች (ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ) ምዝገባ ሥርዓት አስፈላጊነት መሠረታዊ መነሻ በሀገሪቱ ህገ-መንግሥት የተረጋገጡ መሰረታዊ የሰብዓዊ፣ የማህበራዊና ፖለቲካዊ መብቶች ተፈጻሚነትን በቋሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሕጋዊ የማንነት መረጃዎችን ለመንግሥትና ለግለሰቦች በማስገኘት ዜጎች በአገራቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ የልማት ሥራዎች ሙሉ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን መብትና ግዴታ ለማስጠበቅ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ለአንድ ሀገር ፖለቲካዊ አስተዳደር አደረጃጀት፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችን ለመቅረጽ፣ ዕቅዶችንና ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት እንዲሁም እነዚህን ፖሊሲዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ለመፈጸምና የአፈፃፀም ግምገማ እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን ለማድረግ በግብዓትነት የሚፈለጉ የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ ምጣኔ መረጃዎች አግባባዊና ዘመናዊ የመረጃ ምንጭ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ ሥርዓት ነው። የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሰራር በዓለማችን ረጅም ዕድሜን ያስቆጠረ ቢሆንም የምዝገባው ዓላማና የአሰራር ዘዴው ዘመናዊ መልክ በመያዝ በመንግሥት ህግ ተካቶ ዋነኛ የመንግሥት ተግባር የሆነው ከ18ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ ነው።

በመሠረቱ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ዋነኛ ተግባር መረጃ ማመንጨት ነው። ከምዝገባ ሥርዓቱ የሚመነጩ መረጃዎችም በዋነኛነት ለህግ፣ ለህዝብ አስተዳደርና ለስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ ፍጆታ ይውላሉ። በምዝገባ ሥርዓቱ የሚመዘገቡትና የሚሰበሰቡት መረጃዎች በግለሰቦች፣ በማህበረሰብና በመንግሥት ደረጃ በቅንጅት ጥቅም ላይ ለመዋል የሚያስችላቸው የአሰራር ስልት ተነድፎላቸዋል። ይኸም የአሰራር ስልት የሁለት የአመዘጋገብ ሥርዓቶች ጥምረት ውጤት ነው።

እንደተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አጠራር እነዚህ ሁለት ሥርዓቶች የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓትና የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ ሥርዓት በመባል ይታወቃሉ። የእነዚህ ሁለት መረጃ ሥርዓቶች ጥምረት በዋንኛነት በምዝገባ ህግ ዝግጅት፣ አስተዳደራዊና ድርጅታዊ አወቃቀር፣ መረጃ አመዘጋገብና ፍሰት እንዲሁም የአፈጻጸም አደረጃጀት መመሪያ ዝግጅትና አተገባበር ይገለጻል።

በኢትዮጵያ እስከዛሬ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ህግ ካለመደንገጉም በላይ አግባባዊ የወሳኝ ኩነቶች (ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ) ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓቶች አልተቋቋሙም።

## 2. በዓለማችን የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ አሠራር የተጀመረው መቼና እንዴት ነው?

ከዛሬ 300 ዓመት በፊት በሀይማኖት ተቋማት ሲከናወኑ ከነበሩ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓት ማስፈጸሚያ መዝገቦች የወሳኝ ኩነቶች (ቫይታል) ስታትስቲክስ መረጃን ከጤናው ዘርፍ ጋር በማያያዝ ለስታትስቲክስ ተግባር እንዲውሉ የማድረግ ጅምር ተግባሩ የተከናወነው በእንግሊዛዊው ጆን ግራውንት እ.ኤ.አ. በ1662 ነበር። ይኸንኑ ጅምር ተግባር ሳይንሳዊ የአተናተን ስልት እንዲኖረው ለ40 ዓመታት ምርምሮችን በማድረግ ለዘመናዊው ዓለም የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ (Vital Statistics) ሙያንና ቴክኒካዊ አሰራሩን ያበረከተው የመጀመሪያው የእንግሊዝ መረጃ አጠናቃሪ ዶ/ር ዊልያም ፋር የተሰኘ ሰው ነው። በዚህ ረገድ ለወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ሥርዓት ዕድገት ከፍተኛውን ግፊት ያደረገው ተነጻጻሪና ወጥነት ያለው የሞት ምክንያት ዝርዝርን (Uniform classification of cause of death) የማዘጋጀት ፍላጎት ነበር። ለዚህም የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ የስታትስቲክስ ስብሰባ (International Statistical Congress) በብራስልስ እ.ኤ.አ. በ1853 በተካሄደበት ወቅት ለሁሉም ሀገሮች

የሚያገለግል ወጥ የሞት ምክንያት መዘርዝር (Cause of death classification) ከወሳኝ ኩነቶች መረጃ እንዲዘጋጅ መደረጉና ይኸው አሠራር ለጤናው ዘርፍ አግባባዊው የመረጃ ምንጭ እንዲሆን መደረጉ ለሙያው ዕድገት ከፍተኛ ድርሻ ነበረው። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከመቋቋሙ በፊት የተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ለሙያው ዕድገት በርካታ ጥረቶችን ያደረጉ ቢሆንም ድርጅቱ እ.ኤ.አ. በ1945 ሲቋቋም ዓለም አቀፍ ይዘት ያላቸውን ተነጻጻሪ የስታትስቲክስ መረጃዎችን የማመንጨት ሀላፊነቶችን የድርጅቱ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ካውንስል (Economic and Social Council) ሀላፊነቱን እንዲወስድ አድርጓል። በዚሁም መሰረት ድርጅቱ በተለይም ለታዳጊ ሀገሮች የሚሆኑ በርካታ የቴክኒክ መመሪያዎችን በማውጣት ሁሉም ሀገሮች የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃን በየዓመቱ ለድርጅቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያደረገ ይገኛል።

## 3. በዓለማችን አግባባዊ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሠራር የተጀመረው መቼና እንዴት ነው?

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የዛሬውን ቅርጽና ይዘት ለመያዝ በሰው ልጅ ማህበረሰባዊ ታሪክ ውስጥ በርካታ ዘመናትን አስቆጥሯል። የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በተለይም ከሲቪል መብቶች ጋር በመያያዝ በመንግሥት ህግ የተካተተው እ.ኤ.አ በ1804 በወጣው በፈረንሳይ ሲቪል ህግ (Civil Code) ውስጥ በሲቪል ክፍሉ የወሳኝ ኩነቶች (ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ) ምዝገባ አሠራር እንዲካተት በተደረገበት ወቅት ነው። ይኸ የፈረንሳይ ሲቪል ህግ በወቅቱ በምዕራብ አውሮፓ፣ በላቲን አሜሪካ እና በፈረንሳይ ተጽዕኖ ሥር በወደቁት በመካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮች እንዲሰራጭ በመደረጉ በነዚህ ሀገራት ቀደም ሲል በሀይማኖት ተቋማት ሲከናወን የነበረው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በመንግሥታት እንዲከናወንና የመንግሥት ተግባር እንዲሆን በማድረግ ትልቅ መሠረት ጥሏል። በዚህ መነሻ በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ

መሠረቱ እንዲጣል የተደረገው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት በየወቅቱ የሰዎችን መሠረታዊ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች ዕድገትን በመከተልና የቀደምት ሀገሮችን ልምድ በማካተት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሰፊ ጥናትና ምርምር ተደርጎበትና ዓለም አቀፍ ይዘት እንዲኖረው ተደርጎ ዛሬ የዘመናዊው መንግሥት የህዝብ አስተዳደር መርህ አካል በመሆን እያገለገለ ይገኛል።

## 4. ወሳኝ ኩነቶች የሚባሉት እነማን ናቸው?

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ወሳኝ ኩነቶች በመባል የሚታወቁት በህይወት መወለድ (Live Birth)፣ የሽል ሞት (Foetal Death)፣ ሞት (Death)፣ ጋብቻ (Marriage)፣ ፍቺ (Divorce)፣ ጋብቻ እንዳልተከናወነ መቁጠር (Annulment of Marriage)፣ ባልና ሚስትን ለጊዜው በህግ መለያየት (Legal Separation)፣ ጉዲፈቻ (Adoption) እና በህጋዊ ጋብቻ ውስጥ ያልተወለደ ልጅን አባትነት ወይም እናትነት መቀበል (Recognition) ናቸው። የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓትን በአንድ ሀገር በማደራጀት ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ወሳኝ ኩነቶች ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ ናቸው።

## 5. ኩነቶቹ ወይም ክስተቶቹ ወሳኝ የተባሉበት መሠረታዊ ምክንያት ምንድን ነው?

ኩነቶቹ ወሳኝ የተባሉበት መሠረታዊ ምክንያቶች በየሀገሮች ህገ-መንግስትና በዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች የታወቁ መሠረታዊ የሰብዓዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ መብቶችን ተፈጻሚ ለማድረግና መብቶችን ለመጠበቅ ይኸውም ግለሰቦችን ከመንግሥት ጋር በማገናኘት የማንነት መነሻ ህጋዊ መረጃዎች በመሆናቸውና የአንድን ሀገር ህዝብ ብዛትና ዕድገትን የሚወስኑ፣ ለሕብረተሰቡ አልፎም ለግለሰቦች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎችን

ለመቅረጽና ዕቅዶችን በማዘጋጀትና በአፈጻጸማቸው ምሪት በመስጠት ወሳኝ የስነ-ህዝብ መረጃዎች በመሆናቸው ነው።

## 6. የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ትርጉም

የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች አመዘጋገብ አሠራርን በመከተል ማለትም ተከታታይ፣ ቋሚና አስገዳጅ የሆነ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶችንና ከኩነቶቹ ጋር ግኑኝነት ያላቸውን ግለሰቦች የሚመለከቱ የሥነ-ህዝብ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ባህርያትን ለዚሁ ተግባር በተዘጋጁ መዝገቦችና ቅጾች የመመዝገብ፣ የማከማቸት፣ ለሚፈልጉት የህግ፣ የአስተዳደርና የስታትስቲክስ ፍላጎት የማደራጀትና አገልግሎቱን የመስጠት ተግባር ነው።

## 7. የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ ትርጉም

የሕዝብ ብዛት ዕድገት ምጥነትን የሚወስኑ በዋነኝነት የልደትና የሞት እንዲሁም የጋብቻና ፍቺ ኩነቶችን በሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች የአመዘጋገብ ሥርዓት በቀጣይነትና በቋሚነት የመሰብሰብ፣ የማጠናቀር፣ የመተንተንና ውጤቱንም ለኢኮኖሚያዊ፣ ስነ-ህዝባዊና ማህበራዊ ዕቅድ ዝግጅት፣ አፈጻጸምና የአፈጻጸም ግምገማ እንዲሁም ለጥናትና ምርምር ተግባር ስታትስቲካዊ መረጃዎችን የማሰራጨት ተግባር ነው። በየዓመቱና ባነሰ ጊዜ የሚጠናቀሩት ዋነኞቹ የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ መለኪያዎች፡- የልደት ምጥነት (Birth Rate)፣ የጨቅላ ህጻናት ሞት ምጥነት (Infant Mortality Rate)፣ አዲስ ውልድ ሙትት ምጥነት (Neonatal Mortality Rate)፣ ድህረ-ውልድ ሙትት ምጥነት (Post-Neonatal Mortality Rate)፣ የሞት ምክንያት (Cause of Death)፣ የእናቶች ሞት ምጥነት (Maternal Mortality Rate)፣ ግርድፍ ሞት ምጥነት (Crude Death Rate)፣ የህይወት ዘመን ግምት (Life Expectancy at Birth)፣. . . ወዘተ ናቸው።

## 8. የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት ትርጉም

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ በአንድ ሀገር ዜጎች ላይ ከልደት እስከ ዕልፈተ ህይወት የሚከሰቱ ወሳኝ ኩነቶችን (ክስተቶችን) እና ኩነቱ የሚመለከታቸውን ሰዎች የሥነ-ህዝብና ማህበራዊ ባህርያትን፣ የግለሰቦችን ህጋዊ ማንነት በሚያስረዳ አሰራር በቀጣይነትና በቋሚነት በህግ ድጋፍ የመመዝገብ፣ የማከማቸት፣ በየወቅቱ የማደስና በዋነኛነት ለሕግና ለአስተዳደር አፈጻጸም የግለሰብ ወይም ጥቅል መረጃዎችን የማመንጨት እንዲሁም የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃን የማጠናቀርና የማቅረብ፣ እነዚህንም ተግባራት በሀገር አቀፍና በተዋረድ የአስተዳደር ዕርከኖች የሚያስፈጽመውን/ ሙትን ተቋም/ማት በሕግ፣ በአስተዳደርና በድርጅታዊ አወቃቀር የማደራጀት ተግባራትን የሚያጠቃልል የመንግሥት ሥራ ነው።

## 9. የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ዓላማዎች

ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ዓላማዎች በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱት የሚከተሉት ናቸው።

- በሀገሪቱ የገጠርና የከተማ አስተዳደር ዕርከኖች በህግ የተቋቋመ የምዝገባ መዋቅር ዘርግቶ ተከታታይ፣ ቋሚና አስገዳጅ የሆነ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶችን እንደተከሰቱ ህጉ በሚፈቅደው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምዝገባ በማካሄድ ለህግ፣ ለአስተዳደርና ለስታትስቲክስ መረጃ ጥንቅር የሚውሉ ህጋዊና ግለሰባዊ መረጃዎችን ማስገኘት፤
- በምዝገባ ሕጉና ለአመዘጋገቡ በወጣው የምዝገባ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ለተመዘገቡ ኩነቶች ለባለጉዳዮች ህጋዊ የኩነቶች ምስክር ወረቀት መስጠት፤

- ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የተገኙትን ግለሰባዊ የኩነቶች መረጃዎችን ከሕዝብ የክብር መዝገቦች ላይና አስመዝጋቢዎችን በመጠየቅ በተዘጋጁ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ቅጾችን በመሙላት የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎችን ለሚያጠናቅረው፣ ለሚተነትነውና ለሚያሰራጨው አካል መላክ ናቸው።

## 10. የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ ዓላማዎች

- በሕዝብ አስተዳደር፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት አሰጣጥ፣ እንዲሁም በስነ-ሕዝብ ስታቲስቲክስ መረጃ ዝግጅት ዋነኛ ግብዓት የሆኑትን የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ወቅታዊ መረጃዎችን እስከ ትንሹ የአስተዳደር ዕርከን በቀጣይነትና በቋሚነት መሰብሰብ፣ ማጠናቀርና ማሠራጨት፣
- ለሕዝብ ጤና አጠባበቅ እና ለስነ-ሕዝብ ስታቲስቲክስ ጥናትና ምርምር ግብዓት የሚሆኑ የወሳኝ ኩነት ምጣኔ እና ተዛማጅ ስነ-ህዝባዊ መረጃዎችን ማጠናቀር፣ መተንተንና ማቅረብ፣
- በሀገሪቱ የሚካሄደውን የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሠራር የሽፋንና የመረጃ ጥራት ደረጃና አቅርቦቱን ሀገራዊና ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን ስለማሙዋላታቸው ሳይንሳዊ የአጠናን ስልቶችን በመከተል መገምገምና ጥናታዊ ሪፖርቶችን ማቅረብ ናቸው።

## 11. የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባና የስነ-ህዝብ መረጃ አቅርቦት

በስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃ አቅርቦት ዘርፍ ሁለት ዋነኛና መሠረታዊ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ይታወቃሉ። እነርሱም የቆጠራ መንገድ (Enumeration Method) እና የምዝገባ መንገድ (Registration Method) በመባል ተለይተዋል። በቆጠራ መንገድ

የሚካተቱ የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ ያጠናን ዘዴዎች የሕዝብና ቤት ቆጠራዎች (Population and Housing Censuses) እና የስነ-ህዝብ ናሙና ጥናቶች (Demographic Sample Surveys) ሲሆኑ በምዝገባ መንገድ የሚካተቱት ደግሞ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ (Vital Statistics Registration) እና የሕዝብ ምዝገባ (Population Register) ናቸው። እነዚህ የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች በአፈጣጠራቸው፣ በሚያቀርቡት መረጃ ዓይነትና በአጠቃቀማቸው ልዩነትና ተዛምዶ አላቸው። በቆጠራ መንገድ የሚሰበሰቡ መረጃዎች የአንድ ወቅት (stock) የሕዝብ ብዛትን የሚያመለክቱ መረጃዎች የሚገኝበት ሲሆን በአንጻሩ በምዝገባ መንገድ በቀጣይነት (flow)፣ በቋሚነትና በወቅታዊነት የኩነቶች ብዛትና ባህርያት መረጃ ይገኛል። የአንድን ሀገር አጠቃላይም ሆነ በመስተዳድሮች ደረጃ ዓመታዊም ሆነ ከዚያ ባነሰ ጊዜ የሚፈለግን የስነ-ህዝብ መረጃ እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን ለማግኘት በየ10 ዓመት የሚሰበሰበውን የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ በቀጣይነት በምዝገባ ከተገኘው የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ ጋር በማገናኘት መጠቀም የግድ ይላል።

## 12. ወሳኝ ኩነቶች ግለሰብን ከመንግሥት ጋር እንዴት ያገናኛሉ?

መንግሥት ከሚያስተዳድረው ህዝብ ጋር የሚገናኝበት በርካታ መንገዶች እንዳሉት ይታወቃል። ይኸም ሆኖ መንግሥትና ግለሰቦች በቀጥታ ሊገናኙ የሚችሉበት ብቸኛው በመረጃ ላይ የተመሠረተ ህጋዊ አሰራር በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት በሚገኘው ህጋዊና ግለሰባዊ የወሳኝ ኩነቶች (ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ) መረጃዎች አማካይነት ነው። በአንድ ሀገር አግባባዊ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሰራር ከተዘረጋ ሰዎች ከልደት ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ በክብር መዝገብ ሰነድ አማካይነት በመንግሥት ይታወቃሉ። የአንድ አካባቢ ህዝብም በመንግሥትና በግለሰቦች እጅ በሚገኝ ህጋዊ የማንነት የሰነድ መረጃ

አማካይነት ያለ ሶስተኛ ወገን ምስክርነት በቀጥታ ከመንግሥት የህግና አስተዳደር አገልግሎት መስጫ ተቋማት ጋር ይገናኛል። በዚህ ረገድ በኢኮኖሚ በበለጸጉ ሀገሮች በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አማካይነት መንግሥት ዜጎቹን በግለሰብ ደረጃ ከልደት እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ዕለታዊ አኗኗራቸውን ይከታተላል። ይሽንን ሁኔታ የበለጠ ግልጽ ለማድረግ የልደት ኩነትን እንደምሳሌ በመውሰድ እንመልከት፣

- የአንድ ሰው ማንነት ከቤተሰቡ ጀምሮ በመንግሥት የሚለየው በስሙ ነው። ሰዎች በቤተሰባቸው የተሰጣቸው ስም በማናቸውም ጊዜ በማያጠራጥር መልኩ እንዲታወቅና ህጋዊ እንዲሆን በመንግሥት ሰነድ ሊመዘገብ ይገባል። ይሽም የሚሆነው በልደት ኩነት ምዝገባ አሰራር ነው። ለመሆኑ እርስዎ እንደተወለዱ በመንግሥት የልደት መዝገብ የርስዎንና የወላጆችዎን ማንነት በሚለይ አኳኋን ተመዝግበዋል? ማንነትዎን የሚያስጠይቅ የህግ ጉዳይ ቢገጥምዎት በፍርድ ቤት ያለ ሶስተኛ ወገን የሚያረጋግጡበት አስተማማኝ መረጃ አለዎት? ልጆችዎስ እንደተወለዱ በልደት መዝገብ ተመዝግበዋል?

- የልደት መዝገብ ከመለያ ስም በተጨማሪ ህጻኑ በህይወት ዘመኑ የሚገለገልባቸውንና ለዜግነቱ ማረጋገጫ የሚሆኑ የማንነት መረጃዎችን ለምሳሌ የልደት ቀን፣ የልደት ቦታ፣ የወላጆችን ማንነት የሚያረጋግጡ መሠረታዊና ህጋዊ መረጃዎችን እንደተወለደ እንዲኖሩት ያስችላል።

- የልደት ኩነት መመዝገብ ግለሰቦች በማህበረሰብ አባልነት ከአካባቢው የመንግሥት አስተዳደር ማህበራዊና አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚያስችላቸውን ህጋዊ መረጃ

ባለቤት የሚያስደርግ ሰነድ ነው። በሌላ በኩል ህጻናት እንደተወለዱ መንግሥት ባዘጋጀው የልደት መዝገብ ሲመዘገቡ መንግሥት የህጻናቱን መወለድ በመዝገቡ አማካይነት ስለሚያውቅ ህጻናቱ እድሜአቸውን ተከትሎ የሚያስፈልጋቸውን የጤናና የትምህርት ፍላጎት አስቀድሞ ለማቀድ መነሻ የሆነውን መሰረታዊ መረጃ ያስገኝለታል። ይኸም አሰራር ማህበረሰቦችን አልፎም ግለሰቦችን ከመንግሥት ዕቅዶችና አተገባበሮች ጋር በማገናኘት የማስፈጸም አቅምን ያጎለብታል።

## 13. በኢትዮጵያ አገባባዊ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ መኖር በመንግስት የህግና ማህበራዊ አገልግሎት አሰጣጥ የሚያስገኘው መረጃና ጥቅም ምንድነው?

### ሀ. በግለሰባዊ የህግ፣ የአስተዳደርና ማህበራዊ አገልግሎት አሰጣጥ፦

#### *1. በፍትህና የሕዝብ አስተዳደር አገልግሎቶች እንዲሁም ሰብዓዊ መብት ጥበቃ ዘርፍ*

- ✓ እያንዳንዱን በገጠርም ሆነ በከተማ አልፎም ከሀገር ውጭ የሚኖርን ዜጋ በህጋዊ ስሙ በመንግሥት ሰነድ ለይቶ ለማወቅና እያንዳንዱን ዜጋ በሚመለከት ለሚነሱ የህግና የአስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ህጋዊ መረጃ ለግለሰቦችና ለመንግሥት ያስገኛል፤
- ✓ የህፃናት ወላጆች ማንነት በመንግሥት ሰነድ እንዲታወቅ በማድረግ ልጆች ከወላጆቻቸውና ከማህበረሰቡ የሚፈልጉትን አገልግሎት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ያስችላል፤
- ✓ ማንኛውም ሰው በሀገሩ ህግ መሠረት ዜግነቱ በመንግሥት የዜጎች ሰነድ ውስጥ በማያጠራጥር ሁኔታ እንዲመዘገብ ያስችላል፤

- ✓ ስዚጎች የነዋሪነት መታወቂያ በትክክለኛና ህጋዊ መረጃ ላይ በመመሥረት ለማዘጋጀት የሚያስፈልገውን ግለሰባዊ የማንነት መረጃ ያስገኛል፤
- ✓ ልጆችን ከልጅነት ጋብቻ ለመከላከልና ያለዕድሜአቸው ጋብቻ እንዲፈጽሙ ከተገደዱ በህግ ፊት መብታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል ቋሚና ህጋዊ መረጃ ያስገኛል፤
- ✓ ወጣት አጥፊዎች በትክክለኛ ዕድሜአቸው ላይ የተመሠረተ ፍትህ እንዲያገኙ ለማድረግና እውቅና የተሰጣቸውን ሰብዓዊ መብቶች ለማስጠበቅ የሚያስችል ህጋዊ መረጃ ያስገኛል፤
- ✓ ህፃናት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን በእድሜአቸው እንዲጀምሩና መንግሥትም እያንዳንዱ ህፃን ይኸ መብቱ መጠበቁን ለማረጋገጥ የሚያስችለውን ህጋዊ መረጃ ያስገኛል፤
- ✓ ህፃናት ከተወለዱ ጀምሮ ከእናታቸው፣ ከቤተሰቡና ከመንግሥት ሲያገኙ የሚገባቸውን የጤና እንክብካቤ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ቋሚ የመረጃ ሥርዓት ያስገኛል፤
- ✓ ሲወለዱ የአካል ጉድለት ወይም ከልደት ጋር የተያያዙ የጤና ችግሮች ያሉባቸውን ህጻናት የተለየ እንክብካቤ ለማድረግ የሚያስችል ግለሰባዊ መረጃ ከልደት ጀምሮ ያስገኛል፤
- ✓ እናቶች ከወሊድ በኋላ ተገቢውን የህክምና ዕርዳታ ለማግኘት እንዲችሉ የሚረዳ ወቅታዊ ግለሰባዊ መረጃ ለአካባቢ ጤና ተቋማት ያስገኛል፤
- ✓ መንግሥት በህብረተሰቡ ላይ የሚደርሰውን የሞት መጠን የመቀነስ ሀላፊነቱን ለመወጣት እንዲችል የሚረዱ በተለይም በተላላፊ ወይም በወረርሽኝ በሽታዎች የሞቱ ግለሰቦችን ማንነት ሞቱ እንደተከሰተ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ በማስገኘት በአፋጣኝ ተገቢ እርምጃዎችን ለመውሰድ ያስችላል፤
- ✓ በማናቸውም የዕድሜ ክልል የሚፈጸሙ የወንጀል ድርጊቶችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ህጋዊ የማንነት መረጃ ያስገኛል፤
- ✓ በጋብቻ ውስጥ እንዳሉ ወይም ጋብቻው ሲፈርስ የሚከሰቱ የመብት መጣሶችን ለመከላከልና ተገቢውን የአስተዳደርና የህግ ውሳኔ በአፋጣኝ ለማስጠት የሚያስችል ህጋዊ መረጃ ያስገኛል፤

- ✓ አንድ ግለሰብ በመሞቱ ምክንያት ለቤተሰቡ ወይም ለዘመዱ የሚደረጉ የንብረት ውርስ ጥያቄዎችን በህግ ፊት አፋጣኝ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ ህጋዊ መረጃዎችን ያስገኛል፤
- ✓ የአንድ ሀገር ዜጎች ወደ ውጭ ሀገር ለመጓዝ የሚያስፈልጋቸውን ልዩ ልዩ የጉዞ ሰነዶች ለማዘጋጀት የሚያስችል ህጋዊ የማንነት መረጃ በመንግስት ሰነድ ለማስቀመጥ ያስችላል፤
- ✓ የመምረጥና የመመረጥ መብትን ለመጠቀም የእያንዳንዱ ግለሰብ የዕድሜ፣ የዜግነትና ተመሳሳይ የማንነት መረጃዎች በመንግሥት ሰነድ ተመዝግበው እንዲገኙ ለማድረግ ያስችላል፤

## 2. *ማህበረሰብ ተኮር የጤናና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለመስጠት ወቅታዊ መረጃ በማቅረብ*

- ➢ በቀበሌው ውስጥ የተወለዱ ልጆች በተወለዱበት ቀን እና በአድራሻ ዝርዝር፣
- ➢ በቀበሌው ነዋሪ ከሆኑ ወላጆች የተወለዱ ልጆች በተወለዱበት ቀን እና በአድራሻ ዝርዝር፣
- ➢ ሲወለዱ ክብደታቸው ዝቅተኛ የሆኑ ልጆች በተወለዱበት ቀን እና በአድራሻ ዝርዝር፣
- ➢ ሲወለዱ ወይም ከተወለዱ በኋላ የአካል ጉድለት ያለባቸው ህፃናት በተወለዱበት ቀን እና በአድራሻ ዝርዝር፣
- ➢ ሲወልዱ ወይም ከወሊድ ጋር በተያያዘ የሞቱ እናቶች በዕድሜ እና በአድራሻ ዝርዝር
- ➢ በወቅቱ የወለዱ እናቶች ከአሁኑ ልጅ በፊት የወለዱዋቸውና በህይወት ያሉ ልጆች ብዛት እና በአድራሻ ዝርዝር፣
- ➢ የቀበሌ ነዋሪ የሆኑ የወለዱ እናቶች በወሊድ ጊዜ በተደረገ እርዳታ ዓይነት/በወሊድ ቦታ /ሆስፒታል፣በቤት ውስጥ፣ በልምድ አዋላጅ፣.... / እና በአድራሻ ዝርዝር፣

- የቀበሌ ነዋሪ የሆኑ የወለዱ እናቶች በወሊድ ጊዜ ልጆቻቸው የሞቱባቸው በአድራሻ ዝርዝር፣
- የቀበሌ ነዋሪ የሆኑና የወለዱ እናቶች አሁን የወለዱት ልጅ ከቀድሞው ልጅ ያለው የጊዜ ልዩነት በአድራሻ ዝርዝር፣
- የቀበሌ ነዋሪ የሆኑና የመጀመሪያ ልጅ የወለዱ እናቶች በአድራሻ ዝርዝር፣
- በቀበሌው ውስጥ በተላላፊ በሽታ የሞቱ በፆታ እና በአድራሻ ዝርዝር፣
- በቀበሌው ውስጥ ዕድሜአቸው ከ0-4 ዓመት የሆኑ የሞቱ ልጆች በአድራሻ ዝርዝር፣
    - *አድራሻ ሲባል ግለሰቦችን በመኖሪያ ቤት የቤት ቁጥርና መሰል መረጃዎች ለይቶ ለማግኘት የሚያስችል መረጃ ማለት ነው።*

## ለ. በስነ-ህዝብ መረጃ አቅርቦት፤

ከታች የተመለከቱት የስነ-ህዝብ መረጃዎች በአንድ ሀገር አግባባዊ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ ሥርዓት የተዘረጋ ከሆነ ብቻ የሚገኙ ናቸው። በሌላ አገላለጽ እነዚህ በማናቸውም የአስተዳደር እርከን የሕዝብ አስተዳደር መሠረት የሆኑ የስነ-ህዝብ መረጃዎች ሊገኙ የሚችሉት በሀገሪቱ ቀጣይ፣ ቋሚና አስገዳጅ የወሳኝ ኩነቶች (ቫይታል) ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓቶች ሲዘረጉ ብቻ ነው።

### 1. <u>ወርሃዊና የየሩብ ዓመት የመረጃ ፍላጎትን በማሟላት</u> - ከትንሹ የአስተዳደር ዕርከን ጀምሮ

- ✓ በህይወት የተወለዱ ልጆች ብዛት በፆታ፣
- ✓ የወለዱ እናቶች ብዛት በዕድሜ፣
- ✓ የወለዱ እናቶች ብዛት በወለዱበት ቦታ /የጤና ተቋም፣ በቤት ውስጥ፣…/
- ✓ የወለዱ እናቶች ብዛት በመደበኛ መኖሪያ ቦታ፣
- ✓ በህይወት የተወለዱ ልጆች በወላጆች የጋብቻ ሁኔታ፣

- ✓ በህይወት የተወለዱ ልጆች በወላጆቻቸው በህይወት የመኖር ሁኔታ፣
- ✓ በህይወት ተወልደው የሞቱ ልጆች ብዛት በፆታ፣
- ✓ በህይወት ተወልደው የሞቱ ልጆች ብዛት በሞት ምክንያት፣
- ✓ በህይወት ተወልደው የሞቱ ልጆች ብዛት በተወለዱበት ቦታ፣
- ✓ በህይወት የተወለዱ ልጆች ሲወለዱ በነበራቸው ክብደት እና በፆታ፣
- ✓ በህይወት የተወለዱ ልጆች በልደት ዓይነት /አንድ፣መንታ፣ ሶስት፣ .../
- ✓ ሲወለዱ ወይም ከወሊድ ጋር በተያያዘ የሞቱ እናቶች በዕድሜ፣

### 2. *ዓመታዊ የስነ-ህዝብ መረጃ ፍላጎትን በማሙዋላት*

- የየዓመቱን የልደት መጠን እስከ ቀበሌ የአስተዳደር ዕርከን፣
- የየዓመቱን የሞት መጠን/የህፃናትንና የአዋቂዎችን እንዲሁም ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመለየት/እስከ ቀበሌ የአስተዳደር ዕርከን፣
- ለሞት መንስኤ የሆኑ ምክንያቶች መረጃን እስከ ቀበሌ የአስተዳደር ዕርከን፣
- የየዓመቱን የጋብቻ መጠን እስከ ቀበሌ የአስተዳደር ዕርከን፣
- የየዓመቱን የፍቺ መጠን እስከ ቀበሌ የአስተዳደር ዕርከን፣
- የጋብቻ ዕድሜ ስርጭት መረጃን እስከ ቀበሌ የአስተዳደር ዕርከን፣
- ከዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ጀምሮ በተፈጥሮ ክስተቶች (በልደትና ሞት) የሚጨምረውንና የሚቀንሰውን የህዝብ ቁጥር በየዓመቱ አልፎም ባነሰ ጊዜ እስከ ቀበሌ አስተዳደር ለማስላት የሚያስችል መረጃ፤
- የየዓመቱን የህዝብ ብዛት መረጃ እስከ ቀበሌ የአስተዳደር ዕርከን፣

## 14. በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ያለበት ሁኔታ

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት በዋነኝነት የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባን ለህግ፣ ለአስተዳደርና ለስታትስቲክስ የሚያስገኙትን አገልግሎት መሠረት በማድረግ ሁለት የመረጃ አሰባሰብ ተግባራትን ለይቶ የሚያካሂድ የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓት ነው።

እነዚህም ተግባራት የምዝገባ ተግባርና የስታትስቲክስ ተግባር በመባል ይታወቃሉ። በኢትዮጵያ በ1952 ዓ.ም በወጣው የፍትሀ-ብሄር ህግ በምዕራፍ 3 አንቀጽ 47-153 ባሉት ድንጋጌዎች ሥር የክብር መዝገብ ጽሁፎች አዘገጃጀት ሥርዓት በዝርዝር ተመልክቷል። ይሁን እንጂ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባን የሚመለከተው ይኸ ክፍል በሥራ ላይ የሚውልበት ቀን በነጋሪት ጋዜጣ ተወስኖ እስከሚታወጅ ድረስ ተፈጻሚ እንዳይሆን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3361 ተገድቧል። ይኸም ሆኖ የፍትሀ-ብሄር ህጉ የምዝገባ ተግባርን የሚመለከተውን አንዱን የተግባር ዘርፍ ቢይዝም በተጓዳኝ መከናወን የሚገባውን የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ ዘርፍን አላካተተም ነበር። የወሳኝ ኩነቶች መረጃዎች በተለይም የህግ ጉዳዮችንና ሰብዓዊ መብትን በማስፈጸም ካላቸው ሰፊ ድርሻ በመነሳት በ1992 ዓ.ም የጸደቀው የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ በአንቀጽ 321(1) የፌደራሉ መንግሥት ህጉ በሥራ ላይ በዋለ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ህጉ ተፈጻሚ ለሚሆንባቸው መስተዳድሮች የሚያገለግል የምዝገባ ህግ እንዲያወጣና አስፈላጊ ተቋሞችንም እንዲያደራጅ ደንግጓል። በአንድ ሀገር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓቶችን ለማቋቋም ሲታቀድ የሀገሪቱን ህገ-መንግሥታዊ የህግና የአስተዳደር አደረጃጀትን የተከተለና ከዓለም አቀፍ አሰራሮች ጋር የተገናዘበ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ህግ ማውጣት የመጀመሪያ ተግባር አድርጎ መነሳት ይገባል። ከዚህ አንጻር በዘርፉ እየተወሰዱ ካሉ እርምጃዎች ተጠቃሹ በቅርቡ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የቀረበው "ማዕከላዊ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት ለማቋቋምና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ለማደራጀት" የተዘጋጀው ረቂቅ አዋጅ ነው። ይኸም ሆኖ ኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ህግን ካልደነገጉ በጣት ከሚቆጠሩ ሀገሮች አንዷ ከመሆኗም በላይ በሀገሪቱ እስከዛሬ አግባባዊውን የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባም ሆነ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ ሥርዓቶችን በሙከራ ደረጃ እንኳ ያላደረገች ሀገር ነች።

## 15. በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት በሀገሪቱ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓቶችን ለመዘርጋት ምን ጥረቶች እየተደረጉ ነው?

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 103 መሠረት በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 180/91 የተቋቋመ መንግሥታዊ ተቋም ነው። የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ተጠሪነትም ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ነው። እንደሚታወቀው ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት የሰው ሀይልና ድርጅታዊ አወቃቀር መሠረቱ በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን የሕዝብ ጉዳይ ጥናት ማዕከልና የካርቶግራፊ ቡድን ናቸው። በባለሥልጣኑ መ/ቤት የሕዝብ ጉዳይ ጥናት ማዕከል ዋነኛ ተግባር የሕዝብና ቤት ቆጠራ ቴክኒካዊ ሥራዎችን ማከናወን፣ ህዝብ-ነክ ናሙና ጥናቶችንና የቫይታል ስታትስቲክስ መረጃዎችን በተለያዩ የአጠናን ዘዴዎች አማካኝነት ማካሄድ ነበር። እነዚህ የሥራ ዘርፎች ሰፋትና ጥልቀት ተደርጎባቸው የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ዋነኛ የአደረጃጀቱ መነሻና የተግባሩ መሠረት እንዲሆኑ ተደርጓል። በዚህ ረገድ በተለይም የቫይታል ስታትስቲክስ ጥናትና ምርምር መምሪያ ቀደም ሲል በባለሥልጣኑ መ/ቤት በጥራታቸው የተሻሉ የቫይታል ስታትስቲክስ መረጃዎችን የሚያስገኙ የናሙና አጠናን ዜዴዎችን በማካሄድ ላይ ተገድቦ የነበረውን አሠራር በመቀየር በሀገሪቱ የህግ፣ የአስተዳደርና የስታትስቲክስ መረጃዎችን በጣምራ የሚያስገኘውንና በመላ ሀገሪቱ የሕዝብና የቤቶች ምዝገባ አሰራርን ለመዘርጋት መሠረት የሆነውን አግባባዊ የወሳኝ ኩነት ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት የሚቋቋምበትንና የሚያድግበትን ቴክኒካዊ የአሠራር ጥናቶችን እያከናወነ ይገኛል።

## 16. የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባና ያልተማከለ የሕዝብ አስተዳደር ግንባታ

የአንድ ሀገር የልማትና የአስተዳደር ሥርዓት ያልተማከለ በሆነ መጠን በዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን የየዘርፍ ዕቅዶችን ለማዘጋጀት፣ የዕቅዶችን አፈጻጸም ለመከታተልና ለመገምገም እንዲሁም ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያዎችን ለማዘጋጀት በየዘርፉ ጥልቀትና ስፋት ያለው የመረጃ አቅርቦት ሥርዓትን መፍጠር ይጠይቃል። ለዚህም በየትኛውም የአስተዳደር ዕርከን ደረጃ ለሚዘጋጁ የኢኮኖሚና ማህበራዊ የልማት ተግባራት በቀዳሚነት ሊቀርብ የሚገባው መረጃ የስነ-ህዝብ ስታትስቲክስ መረጃ ነው። ይኸውም መስተዳድሮች ከምንም በፊት የሚያገለግሉትን ህዝብ ብዛትና ስብጥር እንዲሁም ምጥነቱን በማያቋርጥ የመረጃ አቅርቦት ሥርዓት ሊያውቁና ሊከታተሉ አልፎም የልማትና የአስተዳደር ዕቅዳቸውና አፈጻጸማቸው መለኪያም መሰረት ሊሆን ግድ ይላል። ይኸ ካልሆነ በየዕርከኑ ያሉ መስተዳድሮች የሚያወጡት ፖሊሲ፣ ዕቅድና ስትራቴጂ ሕዝባዊ መሠረት ሊያጣ ይችላል። በዓለማችን ባለንበት ዘመን ሁሉም ሀገሮች ቢያንስ አንድ ጊዜ የሕዝብና ቤት ቆጠራ አካሂደዋል። ይኸም በአብዛኛው ሀገሮች በየ10 ዓመት የሚካሄደው ቆጠራ የህዝብ ብዛትና ባህርያት መረጃን ቆጠራው ለተካሄደበት ዓመት ብቻ እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን መረጃ ያስገኛል። ትክክለኛና አስተማማኝ የህዝብ ብዛትና ባህርያት መረጃን በቆጠራዎች መሀከል ላሉ ዓመታት ለማስገኘት ለአንድ አካባቢ ሕዝብ ብዛት ለውጥ መንስኤ የሆኑትን የልደትና የሞት ኩነቶች መረጃን ለየዓመቱ ከወሳኝ ኩነት ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት ማግኘት ግድ ይላል። በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ያልተዘረጋ በመሆኑ በክልል ደረጃና በተዋረድ የአስተዳደር ዕርከኖች ወቅታዊ የሕዝብ ብዛትና ባህርያት እንዲሁም የኩነቶች ምጣኔ መረጃዎችን ለየመስተዳድሩ በቆጠራዎች መሀል ላሉ ዓመታት ማቅረብ አልተቻለም። ስለሆነም ኢትዮጵያ እየገነባች ባለችው ያልተማከለ

የሕዝብ አስተዳደር ግንባታ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ ሥርዓትን እስከ ትንሹ የአስተዳደር ዕርከን መዘርጋት አንዱና ዋነኛ የአቅም ግንባታ አካል አድርጎ መውሰድ ግድ ይላል።

## 17. የምዕተ ዓመቱ የልማት ዓላማና የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ መረጃ አቅርቦት

የምዕተ ዓመቱ የልማት መግለጫ በ1992 ዓ.ም ሲጸድቅ በስብሰባው ላይ የተገኙ ሀገራት በጠቅላላው 191 ነበሩ። የምዕተ ዓመቱ የልማት ዓላማ 8 ዓላማዎች፣ 18 ግቦችና 48 ጠቋሚ ማረጋገጫ መለኪያዎችን የያዘ ነው። የምዕተ ዓመቱ የልማት ዓላማዎች በጥቅሉ ሲታዩ ሀገሮች ድህነትን ለማስወገድና ዘላቂ ልማትን ለማምጣት የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በወጥነት ለመለካት የሚያስችሉ የተግባራት ግስጋሴ መከታተያ መሣሪያዎች ስብስብ ናቸው። እነዚህን የተመረጡ ዓላማዎችና ግቦች ከተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ጋር በማያያዝ ለመለካት ትልቁ መሠረት ሆኖ የተቀመጠው መረጃ ነው። የልማት ዓላማዎቹ በሁሉም የልማት ዘርፎች መረጃዎችን ማደራጀት የሚጠይቁ ቢሆንም በተለይም ከዓላማ 1 እስከ 7 ያሉት ዓላማዎችና ግቦች የመረጃ ግብዓት መሠረታቸው የስነ-ህዝብ መረጃዎች መሆናቸው ግልጽ ሊሆን ይገባል። ከዚህም በላይ ዓላማ 4 "የህጻናትን ሞት መጠን መቀነስ"፣ ዓላማ 5 "የእናቶችን ጤና ማሻሻል"፣ እና ዓላማ 6 "ኤድስን፣ ወባንና ሌላም በሽታዎችን ለማስወገድ መታገል" በተሰኙት ሥር የተቀመጡት ግቦችና ጠቋሚ ማረጋገጫዎች አግባባዊው የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ምዝገባ ሥርዓት በሀገር አቀፍ ደረጃ ካልተዘረጋ ትክክለኛና አስተማማኝ መረጃ ማግኘትም ሆነ የተግባራትን ግስጋሴ በሀገር አቀፍና በየአስተዳደር ክልሎችና የማህበረሰብ ክፍሎች በትክክለኛና አስተማማኝ መረጃ ላይ በመመሥረት መለካት አዳጋች ይሆናል። በአጠቃላይ ከምዕተ ዓመቱ የልማት ዓላማዎች ከሁለት ሶስተኛው በላይ ለሚሆኑት የመለኪያ ስሌቶችን በአግባባዊ አሰራር ለማዘጋጀት/

ለማድረግ ቢያንስ ዓመታዊ አስተማማኝ የህዝብ ብዛትና መሰረታዊ የስነ-ህዝብ ባህርያትና ምጥነት መረጃዎችን እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ማደራጀትን ይጠይቃሉ። በመሆኑም በተለይም ኢትዮጵያ ከምትመራው የፌደራል የአስተዳደር አደረጃጀት አንጻር የምዕተ ዓመቱ የልማት ዓላማዎችን ግስጋሴ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሪፖርት ከማዘጋጀት ባለፈ እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ለመለካት የሚያስችል የስነ-ህዝብ መረጃ አቅርቦት ሥርዓት መዘርጋትን ይጠይቃታል።

## 18. ማጠቃለያ

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የመጨረሻ ውጤት ለህግ፣ ለአስተዳደርና ለስታትስቲክስ ጣምራ አገልግሎት የሚሰጡ ግለሰባዊና ጥቅል መረጃዎችን ማመንጨት ነው። እነዚህ በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሰራር ሊገኙ የሚገባቸው ግለሰባዊና ጥቅል መረጃዎች በሌላ በማናቸውም የመረጃ ሥርዓት ሊገኙ የማይችሉ ናቸው። በሌላም በኩል ኩነቶቹ እንደተከሰቱ አንድ ጊዜ በአግባባዊ አመዘጋገብ አሠራር ከተመዘገቡ ሌላ ተጨማሪ መረጃ መሰብሰብ ሳያስፈልግ በዘለቄታ ጥቅም የሚሰጡበት ሥርዓት ነው። በዘርፉ በኢኮኖሚ የበለፀጉ ሀገሮች ልምድ እንደሚያሳየው በአንድ ሀገር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓትን በማቋቋም ሂደት የመጀመሪያ ዓመታት መጠነኛ ወጪን ሊጠይቅ ቢችልም የምዝገባ ሥርዓቱ አንድ ጊዜ በአግባቡ ከተቋቋመ ከሚሰጠው ጥቅም አንጻር ምዝገባው በማህበረሰቡ እንደ ባህል የሚወሰድ ስለሚሆን በትንሽ ወጪ በቀጣይነትና በዘላቂነት የሚካሄድ ነው። ከዚህም በላይ በምዝገባው አሠራር ጥንት አድካሚ የነበረው የዕለት ተዕለት ኩነቶችን የመመዝገብና መረጃዎችን የማከማቸት ሥራ አሁን በዘመኑ በተፈጠሩ የኮምፒውተር ቴክኖሎጂዎች በቀላሉ የሚከናወን በመሆኑ የምዝገባ ሥርዓቱን ለማቋቋም ተነሳሽነቱ ባላቸው ታዳጊ ሀገሮች ሥርዓቱን ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ጥረት በከፍተኛ ደረጃ አቃሎታል። በሌላም

በኩል በኢትዮጵያ እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን የተቋቋሙ የአስተዳደር ተቋማት በተለይም የከተማና የገጠር ቀበሌ መስተዳድሮች የምዝገባ ሥርዓቱ ለሚጠይቀው ድርጅታዊ መዋቅር አመቺ በመሆናቸው ሥርዓቱን የመዘርጋቱንና የማደራጀቱን ሥራ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያቀለው መገመት ይቻላል። ስለሆነም ኢትዮጵያ ለጀመረችው የፌደራልና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መሠረት የሆኑትን ሰብዓዊ መብቶች በአግባባዊ መረጃ ሥርዓት ለመደገፍና ለማስፈጸም እንዲሁም የዘለቄታ ልማትና የድህነት ቅነሳ ስትራተጂ ተግባራዊነት በሀገሪቱ እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን የስነ-ህዝብ መረጃዎችን በቀጣይነትና በቋሚነት ከማቅረብ ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለው ከመሆኑ አንጻር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓቱን በሀገሪቱ የመዘርጋቱን ሥራ የአቅም ግንባታው አካል ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል። ለዚህም በረቂቅ ደረጃ የቀረበውን የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ማቋቋሚያ አዋጅን ሀገራዊና ዓለም ዓቀፋዊ ይዘቱን በማስጠበቅ በአፋጣኝ የሚወጣበትንና ወደ ተግባር የሚገባበትን ስልት መቀየስ እንደሚገባ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ዕምነት ነው። በዚህ ረገድ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት በማቋቋሚያ አዋጁ በዘርፉ የተጣለበትን ተግባርና ሀላፊነቶች መሠረት በማድረግ በሀገሪቱ አግባባዊና ዘመናዊ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓቶችን ለማቋቋም የሚያስችሉ ቴክኒካዊ የጥናት ሥራዎችን በማድረግ ለተግባራዊነቱ የተዘጋጀ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ይገልፃል።

## የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ዓላማዎች

፩. ለአስተዳደራዊ ጉዳዮችና ለምርጫዎች ዕቅድ ዝግጅት፣ ለዕቅድ አፈጻጸም፣ ክትትልና ግምገማ እንዲሁም ለምርምር የሚጠቅሙ ሕዝብና ቤትን የሚመለከቱ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማጠናቀር፣ መገምገምና ማሰራጨት፣

፪. የሕዝብ እና የቤቶች ምዝገባ በመላ ሀገሪቱ እንዲቋቋምና እንዲሰራበት መሠረታዊ ጥናቶችን በማካሄድ የሚደራጅበትን መንገድ መቀየስ፣

*የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ማቋቋሚያ*
*አዋጅ ቁጥር 180/1991፣ አንቀጽ 4*

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግሥት በአንቀጽ 103 ስለ ሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን የተደነገገው

፩. የሀገሪቱን የሕዝብ ቁጥር በየጊዜው የሚያጠናና ቆጠራ የሚያካሂድ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ይኖራል።

፪. የኮሚሽኑ አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ።

፫. ኮሚሽኑ ዋና ጸሐፊ፣ አስፈላጊ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ይኖሩታል።

፬. የኮሚሽኑ ዓመታዊ በጀት በቀጥታ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ይጸድቃል።

፭. የሕዝበ ቆጠራ በየአስር ዓመቱ ይካሄዳል። በውጤቱም መሰረት የምርጫ ክልሎችን አከላለል የምርጫ ቦርድ በሚያቀርበው ረቂቅ መሰረት የፌደሬሽኑ ምክር ቤት ይወስናል።

፮. የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው። ስለ ሥራው አፈጻጸም በየጊዜው ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል።